# MINNESOTA DFL VOTER PROTECTION

# ለመምረጥ ከስራ ፍቃድ ስለማግኘት

## ከደሞዝዎ ምንም ሳይቆረጥ፡ ከግል ወይም ከዓመታዊ ዕረፍትዎ ሳይቀነስ ሂዶ ለመምረጥ ፍቃድ ማግኘት መብትዎ ነው።

የሚመርጡበት ሰዓት ስራ ላይ ባሉበት ግዜ ከሆነ፡ ኣሰሪዎ ለመምረጥ ለሚያስፈልግዎ ግዜ ሊከፍሎት ይገባል። ኣሰሪዎ የግል ግዜዎን ወይም የዕረፍት ግዜዎን እንዲጠቀሙ ሊጠይቅዎ ኣይችልም።

ሂዶ ለመምረጥ የሚያስፈልጎትን ግዜ ብቻ ይውሰዱ። ከዛ በውሃላ ወደ ስራዎ ተመለሱ።

ኣስሪዎ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ ሂደው እንዲመርጡ ሊከለክልዎ፡ ወይም በዚህ መብት ጣልቃ ሊገባ ወይም ለመመረጥ በስንት ሰዓት ላይ መሄድ እንዳለቦ ሊመርጥልዎ ኣይችልም።

ኣሰሪዎ፡ በስንት ሰዓት ላይ ከምርጫው ቦታ እንደምትመለሱ ሊጠይቅ ይችላል። በተጨማሪም ስራ የሚደናቀፍበትን ግዜ ለማሳነስ፡ ሁሉም ሰራተኞች በኣንድ ግዜ እንዳይሄዱ ሊያሳስብ ይችላል።

በማንኛውም የመላው ኣገር፡ በክፍለሃገርና ግዜው በደንብ በታወቀ በኣካባቢ ምርጫዎች ላይ ለመሳተፍ ከስራ ፍቃድ የማግኘት መብት ኣሎት።

## ቅሬታዎች

ይህንን የምርጫ ህግ የሚያፈርስ ኣሰሪ፡ ሕግ በማፍረስ ኣነስተኛ ወንጀል ተከሳሽ ነው። ከሰራተኞች የሚነሳ ቅሬታ በቀበሌው ጠበቃ ጽሕፈት ቤት ሊመዘገብ ይገባል።

## በኣካል ሳይገኙ ወይም ከዋናው የምርጫ ቀን በፊት ለመምረጥ በሚያስችል ወረቀት ኣስቀድሞ መምረጥ

በዋናው የምርጫ ቀን ለመምረጥ ካልፈለጉ ወይም ካልቻሉ ከምርጫው ቀን በፊት ቀደም ብለው መምረጥ ይችላሉ። ከዓርብ መስከረም 21 ቀን ጀምሮ ወደ ምርጫ ጣብያዎ ሂደው በሞሉት ወረቀት ለመምረጥ ይችላሉ። በኣካል መገኘት ለማይችሉ የሚሰጥውን የምርጫ ወረቀትም በፖስታ እንዲላክልዎ መጠየቅ ይችላሉ። የኣካባቢዎ የምርጫ ጣብያ የት እንደሆነ ለማወቅም ሆነ የ ምርጫ ወረቀት እንዲላክሎት መጠየቅ ከፈለጉ mnvotes.gov.ይጎብኙ

## የ2022 ቀናት

ለመምረጥ ተመዝገቡ
በዋናው ምርጫ ቀን፡ ግዜ ለመቆጠብ ቀደም ብለው በግዜ እስከ ጥቅምት *18* ቀን ለመምረጥ ይመዝገቡ።

የምርጫ ቀን
ማክሰኞ ህዳር 8 ቀን

**ለኣሰሪዎ የሚሰጥ ደብዳቤ:**
https://www.sos.state.mn.us/media/3111/letter-to-employers-from-secretary-simon.pdf



**More Information:**
https://dfl.org/voterprotection/ | https://mnvotes.gov | https://iwillvote.com/
1-833-DFL-VOTE